NAFYAD SCHOOL

1SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 2ND LANGUAGE 1

መመሪያ አንድ ፦ ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የያዘውን ፊደል መርጠህ/ሽ በመልስ መስጫ ላይ አጥቁር/ሪ

1. ወዳጅ
   A. ጠላት B. ጓደኛ C. ደመኛ D. ወንድም
2. መላ
   A. ተንኮል B. ምክንያ C. ዘዴ D. A እና B መልስ ናቸው
3. አፋፍ
   A. መሐል B. አፍ C. ውስጥ D. ከፍታ ላይ
4. በራ
   A. ብርሃን ሰጠ B.ሻማ C. ኩራዝ D.ጨለማ ሆነ
5. ውጥን
   A. ጅምር B. ያለቀ C. መጨረሻ D. ፅሑፍ

መመሪያ ሁለት፦ ከዚህ CD ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሺ

6. ነጋ
   A. ዛሬ B. ነገ C. እኩለለሊት D. ጨለመ
7. እርጥብ
   A. ደረቅ B. መካከለኛ C. የራስ D.ውሃ ያዘለ
8. ወፈረ
   A. ደነደነ B. ደለበ C. ከሳ D.ረዘመ
9. ተከለ
   A. አፀደቀ B. ነቀለ C. ኮተኮተ D. ሁሉም መልስ ናቸው
10. ግልፅ
    A. ድብቅ B. ገሃድ C. ቅርብ D.የሚታይ
11. ፍቅር
    A. መዋደድ B. ፀብ C. መስማማት D. መታረቅ
12. ደማቅ
    A. አዲስ B. ቀይ C. ፈዛዛ D. ነጭ

መመሪያ ሶስት ፦ ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ወይም ሀረጎች አግባባዊ ትርጉም ምረጥ/ጪ

13. ለተማሪዎቹ ውጤት መቀነስ <u>መንስኤው</u> ያለማጥናታቸው ነው ።
    A. ምክንያት B. ሰበብ C. መፍትሔ D. A እና B መልስ ናቸው
14. አይጣ ጎተራውን <u>በስታ</u> እህሉን በላች።

A. ሸንቁራ B. ተርትራ C. ከፍታ D. ሰርቃ

15. ድርቅ ረሃብን <u>ሊያስከትል</u> ይችላል።

A. ላያመጣ B. ሊያመጣ C. ሊያጠፋ D. ሊጨምር

16. በአካባቢያችን የተከሰተውን አደጋ ሲያይ <u>ከው አለ</u>።

A. ደነገጠ B. ተከፋ C. ዝም አለ D.ቦዘነ

17. ህፃኑ አሻንጉሊቱ <u>በፈገግታ</u> ተቀበለ።

A. በድንጋጤ B. በግዴለሽነት C. በደስታ D. በቁጣ

18. ተማሪዎቹ ክፍላቸውን <u>አፅድተው</u> ወጡ። የተሰመረበት ቃል ፍቺ

A. ባዶ አድርገው B. ንፁህ አድርገው C. ሙሉ አድርገው D.አቆሸሸው

19. <u>አንጋፋው</u> ተጫዋች ተሸለመ።የተሰመረበት ቃል ፍቺ

A.አጥቂ B. ዝነኛ C. ደካማው D. ዝምተኛ

20. ፊይሳ የያዘው ዱላ <u>ገዳዳ</u> ነው። የተሰመረበት ቃል ተቃራኒው

A. ቀጥ ያለ B. ጠማማ C. ጠንካራ D. ቀጭን

መመሪያ አራት ለባዶ ቦታው ተስማሚ የሆነውን ቃል ምረጥ/ጪ

21. ለጫልቱ አዲስ ልብስ ተገዝቶላታል።---------አልተደሰተችም።

A. ይሁን እንጂ B. እና C. ባይሆንም D.ደግሞ

22. ፌኔት -------- ቶሎሳ የ 8 ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው።

A.ወይም B.ስለሆነ C. እና D.ስለዚህ

23. ለአካለ መጠን --------

A. ሆነ B. አደገ C. ደረሰ D.ተዘጋጀ

24. የከብቶች ማደሪያ ------- ይባላል።

A. ጎረኖ B.ጎጆ C. ጋጣ D. በረት

25. ጠጅ ይጣላል ካልን ጠላ ---------- እንላለን።

A. ይለወሳል B. ይፈላል C. ይጣዳል D. ይጠመቃል

26. ቶላ ማሩ ከቀፎ ውስጥ -------

A. አወጣ B. ቆረጠ C. ጨመረ D. ቀዳ

1SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 2ND LANGUAGE 1

27. ገዛ ብሎ አገዛዝ ካለ ዓፈ ብሎ ------- ይላል

A. ፅሑፍ B. መግፍ C. አግግፍ D .ፀሐፊ

መመሪያ አምስት ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ተስማሚውን ስርአተ ነጥብ በመምረጥ መልስ/ሺ

28. ዛሬ ከትምህርት ቤት ለምን ቀረህ---------

A. ? B. ። C.፡ D. !

29. አባቴ ጎበዝ ገበሬ ነው---------

A. ! B. ። C. ፡ D. –

30. ወይኔ ---------- ቦርሳዬ ተሰረቀ።

A. ፣ B.፡ C. ! D.።

31. መምህሩ ጠንክራችሁ ተማሩ አለ።

A. ‹‹ ›› B. ፤ C. ፣ D.፡

32. ማረፍ እፈልጋለሁ -ቢሆንም ስራዬን አልጨርስም።

A. ፣ B. ፤ C. ! D.።

መመሪያ ስድስት በጅምር የቀሩትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚያሟሉትን አባባሎች ምረጥ/ጪ

33. ብርሌ ከነቃ ----------።

A. ይሰነጠቃል B. ተወዳጅ ይሆናል C. ይሰበራል D.አይሆንም እቃ

34. የነቶሎ ቶሎ ቤት----------።

A. ፈረስ B. ቆርቆሮ ቀረበ C. ግርግዳው ሰንበሌጥ D.ግርግዳው ይሰነጠቃል

35. የጅብ ችኩል ----------።

A. አህያ አገኘ B. ቀንድ ይነክሳል C. ባት ይነክሳል D.እግር ይነክሳል

36. ከልጅ ልጅ ቢለዩ ----------።

A. አመትም አይቆዩ B. ይጣላሉ C. ይመረቃሉ D. ይረገማሉ

37. የቆጡን አወርድ ብላ --------።

A. ወደቀኝ B . የብብቷን ጣለች C. ዘለለች D. ቁጭ አለች

38. ላለፈ ክረምት --------።

A. ቤት አይሰራም B. እህል አይዘራም C. አይገዛም D.አይሰጥም

39. ላም ባልዋለበት ----------።

A. ሳር ፍለጋ B. ውሃ ፍለጋ C. ኩበት ለቀማ D.እንጨት ለቀማ

40. ሲያዩት ያላመረ ---------።

A. ሲበሉት ያቅራል B. ያጠግባል C. ይጣፍጣል D. ያወፍራል

NAFYAD SCHOOL

1SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 2ND LANGUAGE 1

መመሪያ ሰባት ከታች ለቀረቡት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ትክክለኛውን ትርጉም በመምረጥ መልስ/ሺ

41. ሆድና ጀርባ

A. ፍቅረኛሞች B. የሚዋደዱ C. የማይዋደዱ D. A እና B *መልስ* ናቸው

42. ሁለት ፀጉር አወጣ

A. ተበሳጨ B. አረጀ C. ተማረ D.*ተረጋጋ*

43. *መርዘ* ያዘ

A. ክፉኛ ጠላ B. ወደደ C. አከበረ D.*ተዛመደ*

44. አልጫ

A. የዋሃ B. ቸር C. ደፋር D.*ፈሪ*

45. በእንባ ተራጨ

A. ተሰነባበቱ B. ላቁ C. ተላቀሱ D. ተነፋፈቁ

መመሪያ ስምንት ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ልዩ የሆነውን ምረጥ/ጪ

46. A. የጆሮ ጌጥ B. ሐብል C. አንባር D. ሰአት

47. A. ጀልባ B. ታንኳ C. *መርከብ* D. አውሮፕላን

48. A. ደብተር B. ቦርሳ C. *መፅሐፍ* D. ስሃን

49. A. ባህር ዛፍ B. ጥድ C. ማንጎ D. ወይራ

50. A. ድ*መት* B. ህፃን C. አዛውንት D. ጎልማሳ

መመሪያ ዘጠኝ ፡- ቀጥሎ የቀረበውን ግጥም መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ

<u>ጦጣና *መፅ*ር</u>

አንዲት ጦጣ ያረጀች

አይኗ ደክሞ ታወከች

ከሰዎቹ ስምታ ወሬ

*መ*ፍትሐ አለው ብላ አጅሬ

ግማሽ ደርዘን *መ*ነፅር

ገዝታ ሄደች ወደዱር።

NAFYAD SCHOOL

1SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 2ND LANGUAGE 1

ምንጭ -ከመፅሔት

51. ግጥሙ ስንት ስንኝ አለው?

A. 5 B. 6 C. 4 D.12

52. ግጥሙ ስንት ሐረግ አለው?

A. 11 B. 12 C. 10 D.8

53. የግጥሙ ቤት ‹ሬ› የሚያልቀው በስንተኛው ስንኝ ነው?

A. በ 2 እና በ 3 B. በ 4 እና በ 5 C. በ 1 እና በ 2 D. በ 3 እና በ 4

54.አይኗ ደክሞ <u>ታወከች</u> የተሰመረበት ቃል ፍቺ ------- ነው።

A.ፈነጠዘች B. ተደሰተች C. ተረበሸች D. በ 3 እና በ 4

55. ገዘታ ሄደች ወደ <u>ዱር</u>።የተሰመረበት ቃል ፍቺ ------ ነው።

A. ጫካ B. ከተማ C. ገጠር D.ባላገር

ምንባብ

ኢትዮጵያ በጣም <u>ብርቅዬና ድንቅዬ</u> የሆኑ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች የሚገኙባት አገር ናት። ይሁን እንጂ እስከ ዛሬ ድረስ ከቱሪዝም ልታገኘው የቻለችው ገቢ <u>እፍ ሞልተው የሚናገሩት አይደለም።</u> ከቱሪዝም ገቢ አንፃር የኛን ኬንያ ታንዛኒያን ከመሳሰሉት ጎረቤት አገሮች ጋር ስናነፃፅረው አሳዛኝና በጣም አነስተኛ ሆኖ እናገኘዋለን። በሰሜን አፍሪካ ከሚገኙ ግብፅ ቱኒዚያና አልጄሪያ ጋር <u>ስናወዳድር</u> ደግሞ ቱሪዝም ባገራችን <u>የለም ያሰኛል</u>።

ምንጭ ከ *5-8* አጋዥ መፅሐፍ

መመሪያ አስር ፦ ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ መልስ/ሺ።

56. ምንባብ ከስንት አንቀፅ የተገነባ ነው?

A. ከ 3 B. ከ 7 C.ከ 1 D.ከ 4

57. ‹‹ብርቅዬና ድንቅዬ›› የሚላቸው ምንድን ናቸው?

A. እንስሳትና አእዋፍ ናቸው

B. የጅማ አባጅፋር ቤተመንግስት

C. ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ መስቦች ናቸው

D. ሁሉም መልስ ናቸው

58. ‹‹እፍ ሞልተው የሚናገሩት አይደለም ›› የሚለው ምንን ነው ?

A. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶችን ነው።

B. ከቱሪዚም የሚገኘው አነስተኛ ገቢ ነው።

C. የቱሪስት መስህቦችን ነው።

D. መልሱ አልተሰጠም

59. ስናወዳድር ሲል --------- ማለቱ ነው።

A. ስናነፃፅር B. ስናያይዝ C. ስናውቅ D. ሳናይ

60. ‹‹የለም ያሰኛል›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

A. መኖሩን ያመለክታል

B. አጥጋቢ አይደለም ማለቱ ነው

C. ዋስትና የለውም ማለቱ ነው።

D. A እና B መልስ ናቸው።